ቁጥር፡- አ1162/11/15349

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

[illegible] 17 2017

**ለህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት)**

**<u>መቐለ</u>**

**ጉዳዩ፡- <u>ፓርቲው ማድረግ ስለሚገባው ጠቅላላ ጉባኤን ይመለከታል፤</u>**

ህወሓት በኢትዮጵያ የምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነምግባር አዋጅን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 1332/2016 መሠረት በልዩ ሁኔታ መመዝገቡ ይታወቃል።

በአዋጅ ቁጥር 1332/2016 አንቀጽ 3 መሠረት በልዩ ሁኔታ የተመዘገበ ፓርቲ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የፓርቲውን ጠቅላላ ጉባኤ እንዲያደርግ ያዛል። ቦርዱም የፓርቲውን በልዩ ሁኔታ መመዝገብ ባሳወቀበት ነሀሴ 3 ቀን 2016 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ቁጥር አ1162/11/15180 በግልፅ እንዳስቀመጠው ፓርቲው ይህው ደብዳቤና የምዝገባ ሰርትፊኬት ከደረሰው አንስቶ ባሉት ስድስት ወራቶች ውስጥ የቦርዱ ታዛቢዎች በተገኙበት ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባውን ማድረግ እንዳለበት አስታውቋል።

በሌላም በኩል አዋጅ ቁጥር 1332/2016 ዓ.ም ለማስፈፀም ባወጣው መመሪያ ቁጥር 25/2016 አንቀፅ 12 መሰረት በተጠቀሰው አዋጅ መሰረት በልዩ ሁኔታ የተመዘገበ የፓለቲካ ፓርቲ ምዝገባውን ካገኘበት ጊዜ አንስቶ በመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት ጠቅላላ ጉባኤ ማድረግ እንዳለበት ያዛል።

ፓርቲው ከፍ ብሎ የተመለከተውን የአዋጁንና የመመሪያውን ድንጋጌዎችና ቦርዱ ልዩ ምዝገባ ሰርትፊኬቱን ሲሰጠው በፃፈው ደብዳቤ ላይ የተገለፀውን በስድስት ወር ውስጥ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲያደርግ የሚለውን ግዴታ ያለተጨማሪ ማሳሰቢያ መፈፀም እንዳለበት የሚታመን ቢሆንም ቦርዱ ለፓርቲው ነሀሴ 3 ቀን በቁጥር አ1162/11/15180፣ ነሀሴ 20

ለድምጽዎ የሚያምኑን

ፌስቡክ
/national-electoal-boa
of-ethiopia-nebe
ትዊተር
@NEBEthiopia
ኢሜይል
contact@nebe.org.e
ድረ - ገጽ
www.nebe.org.et

አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚንን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ
+251 115 153468

ፋክስ
+251 115 510025

ቀን 2016 ዓ.ም በቁጥር አ1162/11/15209 እና ጥቅምት 21 ቀን 2017 ዓ.ም በቁጥር አ1162/11/15278 በፃፋቸው ደብዳቤዎች ላይ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት በማከናዎን ጠቅላለ ጉባኤውን እንዲያደርግ አስታውቋል።

ፓርቲው በልዩ ሁኔታ የተመዘገበው ነሀሴ 3 ቀን 2016 ዓ.ም በመሆኑ ጠቅላላ ጉባኤውን እስከ የካቲት 3 ቀን 2017 ዓ.ም እንዲያደርግ ይጠበቃል። በሌላ በኩልም ለዚሁ የጠቅላላ ጉባኤ ዝግጅት የሚያስፈልገውን የቅድመ ጉባኤ ዝግጅት የተመለከቱ ስራዎችን ቦርዱ መከታተል እንዲችል ፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤውን ከማድረጉ 21 ቀናት በፊት ጉባኤው የሚደረግበትን ቀን ለቦርድ እንዲያሳውቅ የሚጠበቅ ነው። ይሁንና ይህ ደብዳቤ እስከተፃፈበት ቀን ድረስ ፓርቲው ከተመዘገበ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ጠቅላላ ጉባኤ ማድረግ የሚያስችለውን እንቅስቃሴ እያደረገ መሆኑን ቦርዱ አያውቅም።

በመሆኑም ፓርቲው በልዩ ሁኔታ ከተመዘገበበት ከነሀሴ 3 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ጠቅላላ ጉባኤ ማድረግ የሚገባው ወቅት ሊገባደድ ከሁለት ወር ያነሰ ጊዜ የቀረው በመሆኑ ፓርቲው ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት በልዩ ሁኔታ በተመዘገበበት አዋጅ፣ አዋጁን ለማስፈፀም የወጣው መመሪያና ቦርዱ ከነሀሴ 3 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ በተለያየ ጊዜ ለፓርቲው በፃፈው ደብዳቤዎች ላይ የተሰጡ ውሳኔዎች በማክበር በቀረው አጭር ጊዜ የጠቅላለ ጉባኤውን እንዲያደርግ ቦርዱ በጥብቅ ያስታውቃል።

ይህ በሕግ ፓርቲው ላይ የተጣለ ግዴታ በወቅቱ ሳይፈፀም ቢቀር ቦርዱ ሕጉን መሠረት በማድረግ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን ከወዲሁ በአክብሮት ያስገነዝባል።

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር

ሜላትወርቅ ኃይሉ
የኢትዮጵያ ብሔራዊ
ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ